# የመጨረሻ ሪፖርት ማጠቃለያ

The AMIF ABM3 New Scots: የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ አካታችነት መንገዶች ፕሮጀክት ከንግስት ማርጋሬት ዩኒቨርሲቲ ለዓለም አቀፍ ጤና እና እድገት እና በስኮትላድ ውስጥ ለስደተኞች ልዩ አገልግሎቶችን በመስጠት ላይ ካሉ ሦስት ድርጅቶች የተወጣጡ ተመራማሪዎች አጋርነት ነው[1]:- የስኮቲሽ የስደተኞች ምክርቤት፣ የሰራተኞች የትምህርት ማህበር እና ብሪጅ ፕሮግራሞች። የፕሮጀክቱ የምርምር ይዘት የሚከተሉትን የምርምር ጥያቄዎች ያስሳል:-

- በስደተኞች ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ አካታችነት መንገዶች የማህበራዊ ትሥሥሮች ሚና ምንድን ነው?
- በእነዚህ ሂደቶች ስደተኞች በተለያዩ ደረጃዎች ስለ ትሥሥሮች ያላቸው ግንዛቤ ምንድን ነው?

ምርምሩ፣ በቅርብ የታወቁ ስደተኞችን እና ተሳታፊዎችን ለማሳተፍ ባለብዙ-ዘዴ የማህበራዊ ትሥሥሮች የማዘመድ መሣሪያን፣ የሚታዩ የማዛመድ ሥራዎችን እና ቃለ መጠየቆችን ጨምሮ የተቀላቀሉ-ዘዴዎች ስልትን ይጠቀማል።

## ቁልፍ ግኝቶች

ማህበራዊ ትሥሥሮች ስደተኞችን በማቀላቀል ሂደት በርካታ እና እርስ በርስ የተገናኙ ሚናዎች እናሏቸው ግኝቱ አረጋግጧል። ይህም ግንኙነቶች በሚኖራቸው ቅርፅ፣ በሰዎች ህይወት ላይ በሚኖራቸው ተግባራት እና እንደ የግል ሁኔታቸው፣ ችሎታቸው እና ፍላጎቶቻቸው የሚለያይ ሆኖ ግንኙነቶች ለእነርሱ በሚሰጡት ትርጉም ላይ ይወሰናል። እነዚህ ክፍሎች በሙሉ የስደተኞችን ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ አካታችነት ለመረዳት እና ለማገዝ ወሳኝ ናቸው።

### ግንኙነቶችን መረዳት:- ከብዛት ጥራት

ስደተኞች መረጃ የሚሰጡ፣ ለአስፈላጊ ግብዓቶች እና ለቁልፍ አገልግሎቶች ወይም ድርጅቶች አገናኞች ግንኙነት አስቻይ የሆኑ ትሥሥሮችን ትልቅ ግምት ይሰጣሉ። እነዚህ የተግባር ሚናዎች በመደበኛ ድርጅቶች ብቻ የሚሰሩ አይደሉም። መደበኛ ያልሆኑ ትሥሥሮች እና የቅርብ ጓደኝነቶችም በእኩል ደረጃ ጠቃሚ ናቸው። እምነትን መነሻ ያደረጉ ድርጅቶች ለበርካታ ስደተኞች ቁልፍ ትሥሥሮች ናቸው። አምልኮት መፈፀምን ያስችላሉ እንዲሁም እንደ መገናኛ ቦታዎች ያገለግላሉ፣ አስፈላጊ ነገሮችን ያቀርባሉ፣ የበጎ አድራጎት ዕድሎችን እና የእንግሊዝኛ ቋንቋን የማሳደጊያ ዕድሎችን ይፈጥራሉ።

በትሥሥሮች ላይ ያለ ዕምነት ሰዎችን በክብር በመያዝ ይጎለብታል። በመተማመን ላይ የተመሰረቱ ትሥሥሮች በራስ መተማመንን መልሶ ለመገባት እና ቀጣይ የማህበራዊ እና የኢኮኖሚ አካታችነትን ለማሳለጥ አስተዋፅዖ ያደርጋሉ። በተቃራኒው፣ ችላ እንደተባሉ፣ መድሎ እንደሚደረግባቸው ወይም እንደማይከበሩ በተሰማቸው ጊዜ በማዋሃድ ሂደቱ ላይ እንቅፋት ይፈጥራል። ስልታዊ የሆኑ እንቅፋቶች በሚኖሩ ጊዜ፣ ወሳኝ የሆኑ ትሥሥሮች የሰዎችን መብቶች ማመላከት ብቻ ሳይሆን የማንቃት ሥራም ይኖራቸዋል። ይህ በቅልቅል አገልግሎት አጋሮች እና በሌሎች የስደተኞች-ዘርፍ ድርጅቶች የሚሰራ ወሳኝ ሚና ነው። እነዚህ የእንክብካቤ ተግባራት እና አጋርነቶች ያለምንም ተፅዕኖ የሚወሰዱ ሳይሆኑ የሰዎችን ለራሳቸው የመከራከር በራስ መተማመን ለማሳደግ እና ለመብቶች እና ለዕድሎች መዳረሻ ለማግኘት ወሳኝነት ያላቸው ናቸው።

[1] ስደተኛ የሚለውን ቃል የምንጠቀመው፣ አሁንም በጥገኝነት ጥያቄ ሂደት ላይ ያሉትን ጨምሮ ዓለም አቀፍ ከለላ የሚጠይቁ ወይም ይህ ከለላ የተሰጣቸውን ማናቸውንም ሰዎች ነው።

## ማህበራዊ ትሥሥሮችን መገንባት በማቀላቀሉ ሂደት ሁሉንም ተሳታፊዎች ያሳትፋል

ሥርዓታዊ መሰናክሎች በሚኖሩ ጊዜ፣ የስደተኛ-ዘርፍ ተሳታፊዎች አስፈላጊ ነገሮችን በማሟላት ጉልህ ጊዜ ያጠፋሉ። ይህ በረጅም ጊዜ ዓላማዎች ላይ ይውል የነበረውን ጊዜ ይሻማል። ስደተኞችን በመቀበል የረጅም ጊዜ ታሪክ በሌላቸው የገጠር እና የከተማ አካባቢዎች፣ ልዩ አገልግሎቶች ከሚያቀርቡ ድርጅቶች የሚኖሩ አገልግሎቶችን ጨምሮ በመሰረተ-ልማቶች ላይ ያሉ ክፍተቶች ተጨማሪ የማህበራዊ እና የኢኮኖሚያዊ ውህደት መሰናክሎች ሊፈጥሩ ይችላሉ። ይህም ስደተኞች መብታቸውን በቀጥታ የሚያገኙበት በህግ የተደነገገ ስርዓት የመፍጠርና የማሻሻልን አስፈላጊነት ያሳያል።

## ማህበራዊ ትሥሥሮችን በአገልግሎት አቅርቦቶች ውስጥ ማካተት

ማህበራዊ ትሥሥሮችን ከሌሎች የማዋሃድ ዘርፎች ጋር መወያየት፣ ለምሳሌ ከመጠለያ እና ለሥራ ብቁ መሆን ጋር የበለጠ ውጤታማ ያደርጋል፣ እነዚህን ለብቻቸው ለማየት ከመሞከር ይልቅ። በስም ከሚታወቅ የሥራ ባልደረባ ጋር መተማመን ያለበት ግንኙነት መመስረት የማዋሃድ ዓላማዎችን በአግባቡ ለማሳካት ወሳኝነት አለው። ስደተኞች በጋራ ፍላጎቶች ዙሪያ፣ በማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ወይም በአቻ በሚመሩ ፕሮጀክቶች አማካኝነት፣ ከሌሎች ጋር እንዲገናኙ ዕድሎችን የሚፈጥሩ አገልግሎቶች አወንታዊ ማህበራዊ ግንኙነቶችን ከመፍጠር አኳያ ጠቃሚ ሚናዎችን ይጫወታሉ።

ከምርምር አጋሮች ጋር ትምህርትን መጋራት ሁሉም አጋሮች ሥራቸውን ለውስጥ እና ለውጭ አካላት ምክንያታዊ ማብራሪያ እንዲሰጡ ያግዛል። የምርምር አጋርነቶች ስደተኞች የሚገጥሟቸውን ስርዓታዊ እንቅፋቶች ለመታገልም ወሳኝ መሣሪያዎች ናቸው።

## ጥቆማዎች

- ለሁሉም:-
  - አገልግሎቶች በሚዘጋጁበት እና በሚቀርቡበት ዘርፍ መደበኛ ያልሆኑ ማህበራዊ መስተጋብሮች እንዲፈጠሩ ማገዝ።
- የወደፊት የማዋሃድ አገልግሎቶች:-
  - የሰዎችን ጥንካሪዎች የሚለዩ እና የግል ዓላማቸውን እና ፍላጎቶቻቸውን እንዲያሟሉ የሚያግዙ የማዋሃድ ዕቅድ አካሄድን ማካተት አለባቸው።
  - የማዋሃድ ዕቅድ ሂደትን ለብቻቸው ለይቶ ከማየት ይልቅ በሁሉም ዘርፎች ማካተት አለባቸው።
  - መረጃ በመጋራት፣ ትምህርት እና እውቀትን ከልዩ የስደተኛ አገልግሎቶች፣ ከአካባቢ ባለስልጣናት፣ ከማህበረሰብ ቡድኖች እና በስደተኞች ከሚመሩ እንቅስቃሴዎች ጋር ማዋሃድ አለባቸው።
  - በአካባቢ አገልግሎቶች እና ከተለያዩ ዘርፎች እና ክልሎች ጋር አወንታዊ ትሥሥሮችን ለመፍጠርና ለማስቀጠል መዋዕለ ንዋይ ማፍሰስ አለባቸው።
- የአካባቢ ባለስልጣናት እና የህግ አገልግሎቶች:-
  - መረጃ ለማጋራት እና ውጤታማ የሆነ የማስተላለፍ ሥራን ለመስራት የድጋፍ አውታረ መረቦችን በመላው ስኮትላድ ካርታ ላይ ለማስፈር አለባቸው።

- ○ አገልግሎቶችን ለተለያዩ የአካባቢ አውዶች ለማስተካከል እንዲቻል ከልዩ ባለሙያዎች፣ ከስደተኞች እና ከማህበረሰብ ቡድኖች ጋር መስተጋብር መፍጠርን መቀጠል።
- የስኮትላንድ መንግስት አሁን ያሉ የአዲስ እስኮትስ መዋቅሮችን እንደሚከተለው መጠቀም አለበት፡-
  - የወደፊት የማዋሃድ አገልግሎቶችን ለማዋሃዱ ሁሉን ያቀፈ አካሄድን ተግባራዊ ማድረግ የሚያስችል ጊዜ ለመፍቀድ በቂ ገንዘብ መመደብ።
  - ስደተኞች መብቶቻቸውን ራሳቸውን ችለው እንዲያገኙ ለማድረግ የህግ አገልግሎት አቅራቢዎች ማሻሻያዎችን እንዲያደርጉ ማድረግ።
  - በመላው ስኮትላንድ የእንግሊዝኛ ትምህርት የሚውሉ መደበኛ እና ኢ-መደበኛ ዕድሎችን በግብዓቶች መደገፍ
- የዩናይትድ ኪንግደም መንግስት፡-
  - የማዋሃድ እና የስደተኛ መመሪያዎች ሰፊ በሆኑ ማስረጃዎች ላይ የተመሰረተ መሆኑን ማረጋገጥ እና የጥገኝነት መመሪያዎች በማዋሃድ ሂደቱ ላይ ያላቸውን ተፅዕኖ መረዳት።
  - በቅድሚያ ከተወሰኑ ተከታታይ ውጤቶች ይልቅ ማዋሃድን እንደ ሙሉ ሂደት ያካተተ ሥራን በገንዘብ መደገፍ።
- የወደፊት ምርምሮች፡-
  - በባለሙያዎች፣ በስደተኞች እና በተመራማሪዎች መካከል ውይይት ማድረግ የሚያስችል የረጅም ጊዜ የምርምር-ተግባር አጋርነትን መገንባት፣ በምርምር ሂደቱ ውስጥ የባለሙያዎችን እና የስደተኞችን ግብዓት ማካተት
  - የስደተኞች ምርምር ሥራን ስደተኞችን በማስፈር ያነሰ ተሞክሮ ባለባቸው አካባቢዎች ማድረግ።

የመጨረሻ ሪፖርት ማጠቃለያ

Queen Margaret University
INSTITUTE FOR GLOBAL HEALTH AND DEVELOPMENT

## እውቅና መስጠቶች

የምርምር ቡድን በተለያዩ የፕሮጀክት እንቅስቃሴዎች የተሳተፉትን እና ተሞክሯቸውን ለእኛ ያጋሩትን ሁሉ ያመሰግናል። በተጨማሪም ተሳታፊዎችን ለመመልመል፣ የምርምር ዘዴያችንን ለማሻሻል ያገዙንን እና ለፕሮጀክቱ ቀጣይነት ዕይታቸውን ያጋሩንን በስኮቲሽ የስደተኞች ምክር ቤት ባለሙያዎችን፣ የሰራተኞች የትምህርት ማህበርን እና የብሪጅ ፕሮግራምን የሆኑትን ለማመስገን እፈልጋለን። ይህ ፕሮጀክት እውን የሆነው ከአውሮፓ ህብረት የጥገኝነት ፈንድ፣ ከስደተኛነት እና የማዋሃድ ፈንድ በተገኘ ገንዘብ [UK/2020/PR/0104] ነው።

የምርምር ቡድን፡-

ሙሉ ሪፖርቱ እዚህ መገኘት ይችላል፡- [Publications — Migration, Integration, Social Connection (miscintegrationresearch.org)](miscintegrationresearch.org)

የሚያነጋግሩት ሰው፡-

Queen Margaret University
EDINBURGH

scottish refugee council

BRIDGES PROGRAMMES

WEA Adult Learning Within Reach

miscintegrationresearch.org

https://www.qmu.ac.uk/schools-and-divisions/ighd

Migration, Integration and Social Connection Team
Psychosocial Wellbeing, Integration and Protection Cluster
Institute for Global Health and Development
Queen Margaret University, Edinburgh

This work was undertaken as part of the AMIF-funded 'New Scots Integration – A Pathway to Social and Economic Inclusion' ABM3 Project.